# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

## Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም፡-** ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶስት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ
**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.

## ዜና ዘገባ

**ሰኔ 11 ቀን 2003 ዓ.ም**

**የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሑላሪ ክሊንተን እነ መለስን አስጠነቀቁ፤**

**ለሶስት ቀናት የነበረው ጉብኝት በሰዓታት ተጠናቀቀ፤**

**ወያኔ በ2 ቢሊዮን ብር ከባድ የጦር መሳሪያ ከዩክሬን ገዛ፤**

የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሂላሪ ክሊንተን ለሶስት ቀናት በአዲስ አበባ ጉብኝት ያደርጋሉ ተብሎ በወያኔ ሲለፈፍ ቢሰነብትም ድንገት በገቡበት ዕለት ተመልሰው መውጣታቸው ታወቀ።

ሰኞ ሰኔ 6 ቀን 2003 ዓ.ም ረፋዱ ላይ አዲስ አበባ የገቡት ሄላሪ ክሊንተን በአፍሪካ ህብረት የመሰብሰቢያ አዳራሽ ንግግር አድርገው ቀጥሎ ጉዞዋቸውን ወደ ቤተመንግስት በማምራት ጥቂት ደቂቃ ከመለስ ጋር ቆይታ አድርገው ማምሻዋን ተመልሰው መውጣታቸው መለስና ቡድኑን ያላስደሰተ መሆኑ ታውቆዋል።

ለሶስት ቀናት በአዲስ አበባ የስራ ጉበኝት ያደርጋሉ ተብሎ በወያኔ ሰፊ ሽፋን ሲሰጥ የሰነበተ ቢሆንም ነገሮች ሁሉ እንደታሰበው ሳይሆን ቀርቶ ድንገት በመጡበት ዕለት ተመልሰው ወጥተዋል።

ሚስ ክሊንተን አዲስ አበባ እንደገቡ በቀጥታ ያመሩት ወደ አፍሪካ ህብረት ፅህፈት ቤት ሲሆን እዚያም እንደደሱ በአዳራሹ ሲጠባበቁ ከነበሩት የአፍሪካ ተወካዮች ጋር ለረዥም ሰዓታት የቆየ ውይይት ከማድረጋቸውም በተጨማሪ ለተሰበሰቡት ንግግር ማድረጋቸውም ታውቆዋል።ከአፍሪካ ህብረት ፅህፈት ቤት በቀጥታ አራት ኪሎ ወደ ሚገኘው ቤተ መንግስት በማምራት ከመለስ ዜናዊ ጋር አጭር ቆይታ በማድረግ ወደ ኤምባሲያቸው እንደሄዱም ለማወቅ ተችሎዋል።

ከመለስ ጋር ውይይት አድርገው ሲጨርሱ ለሀገር ውስጥ እና ለውጭ ጋዜጠኞች ጋዜጣዊ መግለጫ ይሰጣሉ ተብሎ ሲጠበቅ ድንገት ሳይታሰብ ሀሳባቸውን በመቀየራቸው የተነሳ በግቢው ሲጠባበቁ የነበሩትን ጋዜጠኞች ጋዜጣዊ መግለጫ መስጠቱ ተሰርዞዋል ከግቢው ውጡ ተብለው እንደተባረሩ ለማረጋገጥ ተችሎዋል፡፡

በአዲስ አበባ ለሶስት ቀናት ሊያደርጉ ከነበረው ጉብኝት መሀከል በዳግማዊ ምኒልክ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኙ የአሜሪካ የሰላም ጉዋዶች ጋር እና የፌስቱላ ሆስፒታልን የሚጎበኙ የነበረ ቢሆንም ሁሉም በነበረ ቀርቶ በገቡበት ዕለት ተመልሰው እንደወጡ ታውቆዋል፡፡

ሄላሪ ድንገት ሀሳባቸውን የቀየሩት በአፋር ክልል ውስጥ በተከሰተው የእሳተ ገሞራ የረጨው ጭስ የአዲስ አበባን አውሮፕላን ማረፊያን ሸፍኖ አውሮፕላኖች እንዳይነሱ ይከለክላል ከሚል ስጋት እንደሆነ ታውቋል፡፡፡፡

ወደ ኢትዮጵያ ከመምጣታቸው በፊት ዛምቢያና ታንዛኒያ ለሁለት ቀናት ቆይታ አድርገው የነበረ ሲሆን በተለይ በታንዛኒያ ዳሬሰላም ባደረጉት ንግግር ለአፍሪካ መሪዎች የማይጥም መልዕክት አስተላልፈው እንደመጡ ታውቆዋል፡፡

አፍሪካ ውስጥ የውጭ ባለሀብቶችና መንግስታት(መሪዎች) ፍላጎታቸው የአፍሪካን የተፈጥሮ ሀብት መቀራመትና እራሳቸውን ማበልፀግ በመሆኑ አፍሪካ አዲስ የቅኝ አገዛዝ ስርዓት ሰለባ ልትሆን ትችላለች ሲሉ ስጋታቸውን መግለፃቸው ተነግሮዋል፡፡

የአፍሪካ መሪዎች ከውጭ የሚመጡ ፕሮጀክቶችን ወደ ስራ እንዲገቡ ከመፍቀዳቸው በፊት ለህዝባቸው ዘላቂ የሆነ ልማትና ጥቅም ሊያመጣ የሚችል መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው በማለት ሂላሪ ክሊንተን አንዳንድ አገሮች እንደ ግሪሳ ወፍ አፍሪካን መውረራቸውን ተቃውመዋል፡፡

በቅኝ አገዛዝ ዘመን እንዳየነው ወደ አፍሪካ መምጣት በጣም ቀላል ነው፡፡ የተፈጥሮ ሀብቶችን እየጫኑ ማግበስበስና መውሰድም እንደዚሁ ቀላል ነበር፡፡ መሪዎች ጋር እየተመሳጠሩ የህዝቡን ሀብት እየጋጡ መሰወርም የተለመደ ነበር እንዳለፈው ሁሉ አንዳንድ አገሮች መልካም አስተዳደርን ያላማከለ ስራ በመስራት ላይ ያሉትን እንደሚቃወሙ ገልፀዋል፡፡

ሚስ ክሊንተን አያይዘውም መልካም አስተዳደርን ዝቅ አድርጎ የሚመለከት አካሄድ ፧ከባለሀብቶች(ኢንቨስተሮች) ጋር ብቻ የተቆራኘ ልማት መመልከት እንደማይሹና ባለሀብቶችም ለተፈጠረላቸው አመቺ ኢንቨስትመንት ዕድል ተገቢ ክፍያ መክፈል እንዳለባቸው የተናገሩ ሲሆን ቻይናን በስም ባይጠሩም መልእክቱ ቻይና በአፍሪካ ሀገሮች ላይ የምታደርገውን የውጭ ኢንቨስትመንት እና እርዳታ የሚመለከት ነበር፡፡

የአሜሪካ ከፍተኛ ባለስልጣን ወደ ኢትዮጵያ ሲመጣ ይህ የመጀመሪያው በመሆኑና ይህንኑ ተከትሎ የወያኔ ቡድን የስራ ውጤት እንደሆነ በሰፊው ከፊልም ጋር በተቀናበረ መልኩ ቅስቀሳ ለማድረግ ታስቦ የነበረ ቢሆንም ያሰቡት ሳይሳካ መቅረቱ ለእነ መለስ ዜናዊ የፖለቲካ ኪሳራ እንደደረሰባቸው ይገመታል::

ይህ በእንዲህ እንዳለ ህዝብ በኑሮ ውድነት እግር ከወርች ታስሮ ባለበት እና በርሀብ እያለቀ ባለበት በዚህ ግዜ ወያኔ ከፍተኛ ገንዘብ በመመደብ ከባድ የጦር መሳሪያ መሸመቱ ተጋለጠ:: T-72 የተሰኙ እና እጅግ ዘመናዊ ናቸው የተባሉ 200 ታንኮችን ከዩክሬን በውድ ዋጋ መግዛቱን የመከላከያ ውስጥ አዋቂ ምንጮች አጋልጠዋል::

በቀን አንድ ግዜ መቅመስ ተስኖዋቸው በየስርቻው እየወደቁ ቀና የሚያደርጋቸው ያጡት የሀገሪቱ ዜጎች ቁጥር እያሻቀበ ባለበት በዚህ ግዜ የወያኔ ቡድን የስልጣን እድሜ ማራዘሚያ እንዲሆነው ብቻ ከ100 ሚሊዮን ዶላር በላይ ወጪ በማድረግ ዘመናዊ ታንኮችን ከዩክሬን ገዝቶ ወደ ሀገር ውስጥ ሊያስገባ መሆኑ የመከላከያ ውስጥ አዋቂ ምንጮቹ አጋልጠዋል::

ቁጥራቸው 200 የሚሆኑት ዘመናዊ ባለ ሰንሰለታማው ተሽከርካሪ ታንኮችን ባለፈው ወር ውስጥ ጄኔራል ታደሰ ወረደና ሌላ አንድ ለግዜው ስሙ ያልተጠቀሰ ጄኔራል አብረው ዩክሬን ድረስ በመጉዋዝ ግዥውን የፈጸሙ መሆኑን ያጋለጡት ምንጮቹ በያዝነው ወር ወደ ሀገር ውስጥ እንደሚገቡም ጨምረው ገልጸዋል::

ከ2 ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ ተደርጎ ግዥ የተፈጸመላቸው ታንኮች በልዩ ትዕዛዝ ከቀድሞው ይዞታቸው መጠናቸው አነስተኛ እንዲሆኑና ፈጣን እንቅስቃሴ እንዲኖራቸው ተደርጎ የተሰሩ መሆኑን የጠቆሙት ምንጮቹ በቅርቡ ይሄን ያህል ብዛት ያለው ታንክ ከዩክሬን የገዛ ሌላ ሀገር እንደሌለም የመከላከያ ውስጥ አዋቂ ምንጮች አጋልጠዋል::

የወያኔ ቡድን የስልጣን እድሜውን ለማራዘም ሲል ከህዝቡ ጉሮሮ ላይ እየነጠቀ መልሶ በመሳሪያና በጦር ኃይል እያስፈራራ ለመግዛት እንዲያመቸው በተለያዩ መልኮች እያደራጀ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ የሰሞኑ ታንኮች ግዥ አንዱ እንደሆነ ምንጮቹ አጋልጠዋል::

ባለፈው ዓመት 4.5 ቢሊዮን ብር መደበኛ በጀት ተመድቦለት የነበረው መከላከያ ሚኒስትር ከሌሎች አንገብጋቢና ወሳኝ ከሆኑ ሚኒስትር መስሪያ ቤት በተለየ ሁኔታ ዘንድሮ ከአምናው የ2 ቢሊዮን ብር ብልጫ ተደርጎለት 6.5 ቢሊዮን ብር እንደተመደበለት ለማወቅ ተችሎዋል::

በየዓመቱ ከሚመደብለት በጀት በተጨማሪ በእርዳታና በሌሎች ከሚገኙ ገንዘቦች ይበልጡን ለመከላከያ እየተሰጠ ተቁዋሙን የህዝብ ማፈኛ ለማድረግ እየተሰራ ሲሆን ዛሬ በህይወት እና በሞት መሀከል ያሉ ዜጎች አስታዋሽ አጥተው የወያኔ ቡድን ግን ለመሳሪያ ግዥ ይሄን ያህል ከፍተኛ ገንዘብ መበተኑ የሚያስዝንና ለዜጎች ክብር የሌለው መሆኑን የሚያሳይ ነው ተብሎዋል::

ለአንድ ፌዴራል ሀገሪቱ መክፈል ከምትችለው በላይ ከፍተኛ ገንዘብ እየተከፈለ ከመሆኑም በላይ ለእያንዳንዱ ጄኔራል መኮንን በቦሌ አቅራቢያ በሚገኙ ሰፈሮች ሰፋፊ መሬቶችን ከመስጠት በተጨማሪ የህንጻ መስሪያ ብር እየተመደበ በሀገር እና በህዝብ ሀብት እየተንደላቀቁ የመለስን የስልጣን እድሜ ለማራዘም ብቻ እየሰሩ የሚገኙ ሆድ እንጂ ህሊና የሌላቸው መሆኑ የታወቀ ሲሆን በእነሱም መሀከል ከፍተኛ የጥቅም ሽኩቻ በመኖሩ በአይነ ቁራኛ እርስ በርስ እንደሚተያዩም ምንጮቹ አክለው ገልፀዋል፡፡

በአዲሱ በጀት 117 ቢሊዮን ብር የተመደበና የፀደቀ ቢሆንም አሁን በእጃቸው ያለውና ወደ ስራ የሚገቡበት ገንዘብ 50 በመቶ የማይሞላ ከመሆኑም በተጨማሪ ከውጭ ይመጣል ተሎለ የጠበቁት ገንዘብ መጠን በማነሱ ከፍተኛ አጣብቂኝ ውስጥ የወደቁ በመሆኑ ከሀብታም ግለሰቦች ላይ ቀስ በቀስ በግዴታና በቅጣት እያሉ ለመሰብሰብ ምስጢራዊ ዕቅድ እንዳላቸውም ተጠቁሞዋል፡፡

በተያዘው የበጀት እቅድ መሰረት ለጤና ጥበቃ ሚኒስትር 2 ቢሊዮን ብር ብቻ ሲመደብ ለመከላከያ ግን 6.5 ቢሊዮን ብር መመደቡ ወያኔ ህዝቡንና ሀገሪቱን በጦር ኃይል እና በመሳሪያ አፍኖ ለመግዛት ያለውን የመጨረሻ ህልም እውን ሊያደርግ ቆርጦ መነሳቱን ያሳያል ተብሎዋል፡፡

በመጨረሻም የወያኔ ቡድን በመሳሪያ ኃይል የሚፋለሙትን እና ለስልጣኔ ያሰጉኛል የሚላቸውን የሀገር ውስጥ ተቃዋሚ ቡድኖች ሽብርተኛ የሚል ስያሜ መስጠቱ ታወቀ፡፡

ማክሰኞ ሰኔ 7 ቀን 2003 ዓ.ም በተወካዮች ምክር ቤት ተብዬ በተደረገው መደበኛ ስብሰባ ላይ ሶስት የሀገር ውስጥ እና ሁለት የውጭ ድርጅቶችን ሽብርተኝነት ስያሜ ማፀደቁ ታውቆዋል፡፡

ማክሰኞ ዕለት በተደረገው በዚሁ መደበኛ ስብሰባ ላይ ድንገት በተያዘ አጀንዳ መሰረት በተደጋጋሚ ግዜ በሽብርተኛነት ተግባር ላይ ተሳትፈዋል በሚል የኦሮሞ ነጻነት ግንባር(ኦነግ)፤ የኦጋዴን ብሔራዊ ነጻ አውጭ ግንባር (ኦብነግ) ፤ግንቦት 7 ድርጅትን ከሀገር ውስጥ ሽብርተኛ ናቸው በሚል በምክር ቤት እንዲጸድቅ ማድረጉ ታውቆዋል፡፡

እጅ አውጡ ሲባሉ የሚያወጡ አውርዱ ሲሉዋቸው የሚያወርዱ የወያኔ አባሎች ብቻ በተሰባሰቡበት በዚሁ ምክር ቤት ተብዬ በተደረገ ስብሰባ ላይ ሌሎች ሁለት በሱማሊያ ውስጥ ይንቀሳቀሳሉ የተባሉ ዓለም አቀፍ ህብረተሰብ ጭምር የሚያውቃቸውን ሽብርተኞች አልሸባብንና አልከይዳን መልሶ ሽብርተኛ የሚል ስያሜ ሰጥቶ የወሰነ መሆኑ አነጋጋሪ ሆኗል፡፡፡

የወያኔው ቡድን የሻዕቢያ ቅጥረኛ፤ተላላኪና ጉዳይ አስፈጻሚ ነው እያለ ኦነግን ሲከስስ እና ሲወነጅል የሰነበተ ሲሆን ሰሞኑን 44 ያህል የኦነግ እስረኞች ናቸው የተባሉትን ከእስር በምህረት መልቀቁ ደግሞ ሽብርተኛ ብሎ ስያሜ ከመስጠቱ ጋር የተጣረሰና የተተራመሰ ግራ የሚያጋባ መሆኑ ታውቆዋል፡፡

ለዓመታት በእስር ቤት ሲሰቃዩ የነበሩትና ከ9 ዓመት እስከ ሞት ድረስ ተፈርዶባቸው የነበሩ የኦነግ እስረኞች ናቸው የተባሉትን ባለፈው ሳምንት 41 ያህሉን ሙሉ ለሙሉ ከእስር ሲፈታቸው 3ቱን ደግሞ ከሞት ወደ እድሜ ይፍታህ ዝቅ ማድረጉ ይታወሳል፡፡

በእስር ላይ የቆዩትንና ለዓመታት ሲሰቃዩ የነበሩት 12 እስረኞች ከዝዋይ እስር ቤት ሌሎቹ 29 ደግሞ ከቃሊቲ እስር ቤት ውስጥ በአጠቃላይ 41 እስረኞች ሙሉ ለሙሉ ከእስር ነጻ የተለቀቁ መሆኑ እየታወቀ መልሶ ኦነግን በአሸባሪነት እየወነጀለ መገኘቱ ግራ የሚያጋባ ነው ሲሉም ምሁራኖቹ ይተቻሉ::

ለማስመሰል ብቻ ለብሔራዊ እርቅ እየሰራሁ ነው እያለ ባዶ ፕሮፓጋንዳ እየነዛ ያለው የወያኔ ቡድን አንዳንድ ሃይሎችን በሽብርተኝነት መወንጀሉ ዘላቂ የሆነ ሰላም በሀገሪቱ እንዳይኖርና ሀገሪቱ በሽብር እንድትታመስ ሆን ብሎ እየሰራ ያለ ለመሆኑ ማሳያ ነው ሲሉም ብዙ የሀገሪቱ ህዝቦች እየተናገሩ ይገኛሉ::

ይህንኑ ተከትሎ በአዲስ አበባ በ16ኛው የመሪዎች ስብሰባ ላይ አደጋ ሊጥሉ ሲሉ የተያዙ የሻዕቢያ ቅጥረኛ የሆኑ የኦነግ አባሎች ናቸው ባላቸው 14 ሰዎች ላይ የቅስቀሳ ስራ ሲያደርግ ከመክሰንበቱም በተጨማሪ ሰሞኑን ከ9 ዓመት እስከ እድሜ ልክ እስራት የተፈረደባቸው መሆኑ አይዘነጋም::

ከኦብነግ ጋርም ፍጹማዊ ስምምነት አድርጌያለሁ..... ከእንግዲህም በሀገር ውስጥ እንቅስቃሴ አያደርግም...... ድርጅቱ ከስሞዋል ......ህልውናው አክትሞዋል.......በማለት ለረጅም ቀናት ቅስቀሳ ሲያደርግ ከመሰንበቱም በተጨማሪ በእስር ላይ የሚገኙ የኦብነግ ታጣቂዎችን በምህረት የለቀቀ ሲሆን ከነዚህም መሀከል የመንገድ ትራንስፖርት ሚኒስትር የነበረውን የሱማሌ ተወላጅ አብዱልመጅድ ሁሴን ላይ የመግደል ሙከራ ያደረጉትና በሞት እንዲቀጡ የተወሰነባቸው ጭምር ከእስር መፍታቱ እየታወቀ መልሶ በአሸባሪነት መወንጀሉና በምክር ቤት ማፅደቁ እርስ በርሱ የተምታታ ስራ እየሰራ መሆኑን ከማሳየቱም ባሻገር ወያኔ በውስጡ አድጎና ጎልምሶ የተቀመጠ ፍርሀት እንዳለ ቁልጭ አድረጎ የሚያሳይ ነው ተብሎዋል::